## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 255549

ህዳር 28 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች - ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንደሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ሀይሌ ጸጋዬ- ከጠበቃ ይዘዲን ፈድሉ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አበባ ፍታዊ - ከጠበቃ መኩ ደጉ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር ውርስ እንዲጣራ የቀረበን አቤቱታ እና ለወራሽ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት የሚያስከትለውን ውጤት የተመለከተ ነው፡፡

ክርክሩ የጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች በቀን 27/04/2012 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ አባቴ አቶ ጸጋዬ ታደሰ ውበት በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 07 በቤ/ቁ አዲስ ሲኖሩ ባደረባቸው ህመም ምክንያት መስከረም 12 ቀን 1995 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል፤ ከሳሽ የሟች ወራሽ ልጅ ለመሆኔ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በፍ/ቤት ተረጋግጧል፤ ከሳሽ የሟች አቶ ጸጋዬ ታደሰ ብቸኛ ልጅ ስሆን ተከሳሽ ደግሞ የሟች ባለቤት ነበሩ፤ ስለሆነም የንብረት ክፍፍል ለማድረግ እንድንችል የውርስ ሀብት አጣሪ እንዲሾምልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽ በሰጡት መልስ ከሳሽ የሟች አቶ ጸጋዬ ታደሰን የወራሽነት ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲሰጠው የጠየቀና ያወጣው እንዲሁም ውርስ እንዲጣራና ክፍፍል እንዲደረግም የጠየቀው ሟች ከሞተ 17 አመት በኋላ ነው፤ ይህም የሚያሳየው ከሳሽ በህጉ በተቀመጠው ግዜ ውስጥ የወራሽነት ጥያቄ አለማቅረቡን ነው፡፡ ስለዚህ የከሳሽ ውርስ አጣሪ ይሾምልኝ ጥያቄም ይሁን የውርስ ጥያቄ በግዜው የቀረበ ስላልሆነ በይርጋ ሊታገድ ይገባል፡፡ ከዚህም ሌላ ከሳሽ አቤቱታውን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የለውም፡፡ ምክንያቱም ሟች ከሞተ በኋላ የሟች አባት የነበሩት አቶ ታደሰ ውበት የሟች ወራሽ ነኝ በማለት ወደ ተከሳሽ መጥተዋል፡፡ በግዜው ስፋቱ 75 ካ/ሜ በሆነ ቦታ ውስጥ ከሟች ጋር በጋራ የሰራነው የጭቃ ቤት ነበረን፡፡ የሟች አባት የሟች ወራሽ እኔ ነኝ፣ ሟች ልጅ የለውም በማለት የሟችን ድርሻ እንዳካፍላቸው ሲጠይቁኝ የሟች ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከፍ/ቤት ይዘዋል፡፡ ተከሳሽም እሺ ግማሹ የልጅዎት ድርሻ ነው ይውሰዱ ብዬ ድርሻቸውን ሰጥቻለሁ፡፡ የሟች አባት ድርሻዬ በገንዘብ ተገምቶ ይከፈለኝ እና ለተከሳሽ ልልቀቅላት በማለታቸው ሚያዚያ 4 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት የሟችን ድርሻ በገንዘብ ከፍያለሁ፡፡ ይህንን የሚያረጋጥ በቂ ማስረጃ አለኝ፡፡ ስለዚህ ከሳሽ መብት አለኝ ካለ እንኳ ሊጠይቅ የሚገባው የሟችን ድርሻ የወሰዱትን የሟች አባት እንጂ እኔን ተከሳሽን ለመጠየቅ መብት የለውም፡፡ ተከሳሽ በቅን ልቦና በግዜው የተሻለ ወራሽነት መብት ላላቸው ሰው የሟችን ድርሻ ከፍያለሁ፡፡ ስለዚህ ይህን የተከሳሽን የግል ቤት በተመለከተ ከሳሽ ውርስ ይጣራልኝ ብሎ አቤቱታ የማቅረብ መብትና ጥቅም የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

በፍሬ ጉዳዩም በተመሳሳይ በሰጡት መልስ ሟች በህይወት እያለ ልጅ የለኝም ይል ነበር፤ ልጅ አለኝ ብሎ አያውቅም፤ ልጅ ስለሌለውም ይቆጬ ነበር፤ ሟች ረጅም ግዜ ታሞ በቆየበት ግዜም ይሁን ሊሞት አካባቢ ልጅ አለኝ ብሎ አያውቅም፤ የሟች አባት ከክፍለ ሀገር መጥተው ልጄ ልጅ ሳይወልድ ሞተ በማለት በሀዘን ወቅትም ይሁን ከዛ በኋላ ሲያወሩ ነበር፤ ሟች ልጅ ቢኖረው ኖሮ ራሱም ይሁን ወላጅ አባቱ ስለ ልጁ ይናገሩ ነበር፤ ከሳሽም እውነተኛ የሟች ልጅ ቢሆን ኖሮ 17 አመት ሙሉ ዝም

ብሎ አይቆይም ነበር፡፡ ሟች ከሞተ በኋላ የሟች አባት የነበሩት አቶ ታደሰ የሟች ወራሽ ነኝ በማለት ማስረጃ ከፍ/ቤት ይዘው መጥተው ሚያዚያ 4 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት የሟችን ድርሻ ከፍያለሁ፡፡ ስለዚህ ከሳሽ የሟችን ድርሻ አይወርስም እንጂ ይወርሳል ቢባል እንኳ የእርሱን ድርሻ በቅን ልቦና ለሟች አባት ከፍያለሁ፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ድርሻውን መጠየቅ የሚችለው ከሟች አባት እንጂ ከተከሳሽ አይደለም፡፡ ተከሳሽ የሟችን ድርሻ ከከፈልኩ በኋላ የግል ንብረቴ ስለሆነ ከፍተኛ ለውጥ በማድረግ የባለንብረትነት መብት በያዝኩበት ቤት ላይ ከሳሹ ለንብረት ክፍፍል መሰረት የሚሆን ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት አቤቱታ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም የውርስ አጣሪ ሊሾም አይገባም ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ተከሳሽ ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ በሰጠው ብይን ከሳሽ በወቅቱ ህጻን ስለነበሩ ይርጋው የሚቆጠረው መብታቸውን መጠቀም ከሚጀምሩበት ጀምሮ በመሆኑ በይርጋ አይታገድም፤ ከሳሽን ወክሎ መቀበል ለማይችል ሰው ከመክፈላቸው አንጻርም አሳማኝ ሆኖ አልተገኘም በማለት መቃወሚያውን አልፎ የፍሬ ነገር ክርክሩ እንዲታይ እና ውርስ አጣሪም እንዲሾም አድርጓል፡፡

የውርስ ሀብቱ ተጣርቶም ሪፖርቱ ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ የሟች አቶ ጸጋዬ የውርስ ሀብት በተከሳሽ ስም የተመዘገበ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤ/ቁ አዲስ የሆነ 75 ካ/ሜ ብቻ እንደሆነ በግራ ቀኙ አልተካደም፡፡ በውርስ ማጣራት ስራውም የተገኘው የሟች የውርስ ሀብት ይህ ቤት ብቻ ለመሆኑ በውርስ አጣሪ ሪፖርት ተረጋግጧል፡፡ ተከሳሽ የሟች አባት የሆኑት አቶ ታደሰ ውበት የሟች ወራሽ እንደሆኑ የተሰጠ ውሳኔ በማቅረባቸው ብቸኛ የሆነው የሟች የውርስ ሀብት ያለበትን ይህን ቤት ተከሳሽ እና የሟች ወራሽ የሆኑት ታደሰ ውበት ሚዚያ 4 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት የሟች ድርሻ 3750.00 ብር ተገምቶ የድርሻቸውን የከፈሏቸው ለመሆኑ ተከሳሽ ስምምነቱን አቅርበዋል፡፡ ከሳሽ የሟች ወራሽ እንደሆኑ ማስረጃ በማቅረብ የሟችን ውርስ የወሰዱትን ግለሰብ የወራሽነት ማስረጃቸውን በመቃወም እንዲሰረዝ በማድረግ የወሰዱትን ንብረት እንዲመልሱ ከማድረግ ውጭ ተከሳሽን የሟችን የውርስ ሀብት ድርሻ እንዲሰጧቸው የሚያቀርቡት አቤቱታ በህግ ተቀባይነት ያለው ባለመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ተደርጓል፡፡

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

በዚህም ምክንያት በተከሳሽ ስም የተመዘገበው ቤት የሟች አቶ ጸጋዬ ታደሰ የውርስ ሀብት ተብሎ ሊመዘገብ አይገባም ብለናል፡፡ ስለዚህ በቀን 12/09/2013 ዓ.ም የቀረበው የውርስ ሀብት ሪፖርት ተሻሽሎ ጸድቋል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች በቀን 18/08/2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተፈፀመ የሚሉትን ስህተት ዘርዝረው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የውርስ አጣሪ ያቀረቡትን ሪፖርት ሙሉ በሙሉ በመሻር የራሱን አስቀድሞ የሰጠውን ብይን ሽሮ አመልካችን ከውርስ መንቀሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻርና የውርስ አጣሪ ያቀረቡት ሪፖርት እንዲጸድቅ እንዲወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ቅሬታው ተመርምሮ አከራካሪ የሆነውን የውርስ ንብረት ወራሽነታቸውን አረጋግጠው ድርሻቸውን ለሟች አባት ሰጥቻለሁ ብለው ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር የስር ፍ/ቤት በብይን ውድቅ አድርጎ እያለ በመጨረሻ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ የሟች አባት የውርስ ንብረቱን ተካፍለዋል በሚል የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጉ ትክክል መሆን አለመሆንና አከራካሪ የሆነው ቤት የውርስ ንብረት አይደለም በማለት የተሰጠውን ውሳኔ ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 20/12/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት መልስ በምሰጥበት ግዜም ይሁን በውርስ ማጣራቱ ወቅት የሟችን ድርሻ የወራሽነት ማስረጃ ይዘው ለቀረቡት የሟች አባት በቅን ልቦና ከፍያለሁ በማለት በሰነድና በሰው ማስረጃ የተረጋገጠ ክርክር አቅርቢያለሁ፡፡ በስር ፍ/ቤት በተሰጠው ብይን ተጠሪ የሟችን ድርሻ ለሟች አባት በቅን ልቦና ከፍያለሁ የሚሉ ከሆነ በውርስ ሀብት ማጣራት ሂደት ላይ ተጣርቶ ቀርቦ የሚወሰን ከመሆኑ ውጭ ከወዲሁ የሟችን ውርስ ለማጣራት አመልካች መብትና ጥቅም የላቸውም የሚያስብል አይደለም በሚል መቃወሚያው ውድቅ ተደረገ እንጂ ተጠሪ የሟችን ድርሻ ለሟች አባት ከፍያለሁ በማለት ያቀረብኩት ክርክር ውድቅ አልተደረገም፡፡ ይልቁንም በውርስ ማጣራት ሂደቱ ላይ ተጣርቶ ይወሰናል በሚል ፍ/ቤቱ በሰጠው ብይን አግባብ በውርስ ማጣራት ሂደቱ የስር ፍ/ቤቱ በዚህ ረገድ የቀረበውን ማስረጃ በመመርመር

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

አከራካሪው ቤት የውርስ ንብረት አለመሆኑን በማስረጃ አረጋግጦ ቤቱ የውርስ ንብረት አይደለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቹም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በውሳኔው የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው የስር ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ባሳለፈው ብይን አመልካች በአባታቸው ህልፈት ጊዜ ህጻን ስለነበሩ ይርጋው የሚቆጠርባቸው በመብታቸው መጠቀም ከሚጀምሩበት ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በይርጋ አይታገድም፤ እንዲሁም ውርስ እንዲጣራ ለመጠየቅ የሚያስችል መብት እንዳላቸው ስላሳዩ ተጠሪ አስቀድሞ ለሟች አባት መክፈላቸውን በመጥቀስ አመልካች ክሱን ለማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ያቀረቡት የመቃወሚያ ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ ከማድረጉ በቀር በመቃወሚያው ላይ ባሳለፈው ብይን በፍሬ ነገር ክርክሩ ላይ ውሳኔ ሰጥቶ ነበር የሚሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ከዚህ አንጻር አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ እና ለሰበር ችሎቱ የተያዘው ጭብጥ በስር ፍርድ ቤት የተደረገውን ክርክር እና የተሰጠውን ብይንና ውሳኔ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

ይልቁንም በህጉ አግባብ ወራሽ ነው ለተባለ ሰው የተሰጠ የምስክር ወረቀት ሲኖርና ይህን ተከትሎ በወራሽነት ስም በወራሹ የተፈፀሙ ተግባሮች ያሉ እንደሆነ እነዚህን ተግባሮች ለመቃወም የሚቻልበትን ሁኔታ እና እንዲህ ያለው ክርክር በፍርድ በተያዘ ጉዳይ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ ሊከተለው የሚገባውን ስርዓት በተመለከተ አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በመመርመር ለጉዳይ ዕልባት መስጠቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

እንደሚታወቀው ለወራሽ ስለሚሰጥ የምስክር ወረቀት እና የጸና የወራሽነት ማስረጃ የሚያስከትላቸው ውጤቶች በፍ/ብ/ህ/ቁ 996 እና 997 ስር ተደንግጓል፡፡ ለወራሹ የተሰጠ የምስክር ወረቀት ውጤትን በተመለከተ በፍ/ህ/ቁ 997(1) ስር እንደተደነገገው ለሟች ወራሽ የተሰጠው

የወራሽነት ማስረጃ እስካልተሰረዘ ድረስ ወራሹ በተባለው የምስክር ወረቀት እንደተገለጸው ወራሽ እንደሆኑ ይገመታል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር ደግሞ በወራሽነት ስም በወራሹ የተፈጸሙ ተግባሮች ያሉ እንደሆነ ተግባሮቹ በተፈጸሙበት ጊዜ የተባለው ወራሽ የወራሽነት መብት እንዳልነበረው በግልጽ ማወቁ ካልተረጋገጠ በቀር እነዚህን ተግባሮች ለመቃወም አይቻልም፡፡ ስለሆነም ከድንጋጌው መገንዘብ የሚቻለው የወራሽነት የምስክር ወረቀት በፍ/ብ/ህ/ቁ 996 መሰረት የተሰጠው ሰው ወራሽ እንደሆነ የሚገመት ሲሆን በወራሽነቱ የፈፀማቸውን ተግባሮች ለመቃወም የተባለው ወራሽ ተግባሮቹ በተፈፀሙበት ጊዜ የወራሽነት መብት እንዳልነበረው በግልጽ ማወቁን ማረጋገጥ ይጠይቃል፡፡

በሌላ በኩል በአንድ ጉዳይ ላይ ክስ ሲቀርብና የክሱ ምክንያት የብዙ ሰዎችን መብትና ጥቅም የሚነካ ሆኖ ከእነሱ አንዱ ወይም በከፊሉ ላይ ክስ በቀረበ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጉዳዩ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ መብትና ጥቅማቸው የሚነካ ሲሆን በክሱ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 39/1/ እና 40/2/ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በክሱ መግባት ያለበት በተከሣሽነት የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የክርክር ተካፋይ እንዲሆንና በቀረበው ክስ የመልስ መከላከያውን እንዲያቀርብ ሊያዘው የግድ የሚል ስለመሆኑ የሥነ ሥርአት ህጉ ያሳያል፡፡ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች ማለት ደግሞ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ጥቅማቸው፣ መብታቸው ወይም ግዴታቸው የሚነካ በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች ስለመሆናቸው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የሟች አባታቸው አቶ ጸጋዬ ታደሰ ወራሽ መሆናቸውንና በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 07 በቤ/ቁ አዲስ የሆነው ቤት የውርስ ሀብት በመሆኑ የሟች ሚስት ከሆኑት ተጠሪ ጋር ንብረቱን መከፋፈል እንዲችሉ የውርስ ሀብት እንዲጣራ የሚጠይቅ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ሟች ከሞቱ በኋላ የሟች አባት አቶ ታደሰ ውበት የሟች ወራሽ ነኝ በማለት የወራሽነት ማረጋገጫ አውጥተው ሟች ልጅ የለውም በማለት ቀርበው የውርስ ድርሻ ጠይቀው የወቅቱን የቤቱ የሟች ድርሻ ግምት ሰጥቻለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረቡት ይህ ክርክር በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

*ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ከፍሲል በተጠቀሱት የህጉ ድንጋጌዎች መሰረት የግራቀኙን ክርክር ለመወሰን የሟች አባት አቶ ታደሰ ውበት የሟች ወራሽ ነኝ በማለት የወራሽነት ማረጋገጫ አውጥተው ሟች ልጅ የለውም በማለት ቀርበው የፈፀሙትን ተግባር መቃወምና አቶ ታደሰ ውበት የወራሽነት መብት እንዳልነበራቸው በግልጽ ማወቃቸውን ማረጋገጥ ይጠይቃል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አቶ ታደሰ ውበት በክርክሩ የግድ ተካፋይ መሆን እንደሚኖርባቸው ከክርክሩ ምክንያት እና ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 39/1/ እና 40/2/ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የወራሽነት የምስክር ወረቀት በማቅረብ ክርክር የቀረበበትን የውርሱን ድርሻ አስቀድመው ወስደዋል የተባሉት ሰው ወደ ክርክሩ ባልገቡበትና የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆኑ በጉዳዩ ላይ ውጤታማ ውሣኔ የሚሰጥበት የህግ ምክንያትም የለም፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት አከራካሪ የሆነው የውርስ ድርሻ አስቀድሞ ተከፍሏቸዋል የተባሉት ሰው የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑና መልስ እንዲያቀርቡ ተደርጎ ድርሻ ጠይቀው ወሰዱ በተባለ ጊዜ የወራሽነት መብት እንዳልነበራቸው በግልጽ የሚያውቁ መሆን አለመሆኑን በማረጋገጥ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ አለመስጠቱ ግራቀኝ ያቀረቡትን ክርክር ይዘትና የፍ/ብ/ህ/ቁ 996፣ 997 እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 39/1/ እና 40/2/ ድንጋጌዎችን የተከተለ ባለመሆኑ ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይህን ሳያርም ማለፉ የሚነቀፍ ነው፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 113943 በቀን 27/05/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 287128 በቀን 23/07/2014 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ አከራካሪ የሆነው የውርስ ድርሻ በገንዘብ ተገምቶ አስቀድሞ ተከፍሏቸዋል የተባሉት አቶ ታደሰ ውበት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑና መልስ እንዲያቀርቡ በማድረግ የውርሱን ድርሻ ጠይቀው ወሰዱ በተባለ ጊዜ የወራሽነት መብት እንዳልነበራቸው በግልጽ የሚያውቁ መሆን አለመሆኑን በተገቢው ማስረጃ ሁሉ በማረጋገጥ በአጠቃላይ ክርክሩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰናል፡፡

*ማ ሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

3. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*